## <u>ጋዜጣዊ መግለጫ</u>

## <u>በሞስኮ የኢፌዲሪ ኤምባሲ የቱሪዝም ገጽታችንን የሚያስተዋውቅ የፎቶግራፍ ኤግዚብሽን ፕሮግራም ተካሄደ</u>

እ.ኤ.አ ኦክቶበር 22 ቀን 2015 በሞስኮ የሚገኘው የኢፌዲሪ ኤምባሲ ቱሪቦስ ከተባለው የሩሲያ የአስጎብኚ ድርጅት ጋር በመተባበር  የአገራችንን ተፈጥሮአዊ፣ ባህላዊ አኗኗር እና አለባበስ የሚያስተዋውቁ እና ብዛት ባላቸው ፎቶግራፎች የተደገፈ የፎቶ ኤግዚብሽን ፕሮግራም አካሂዷል:: በዚህ መድረክ ላይ  ቁጥራቸው ከ300 በላይ የሚገመቱ ሩሲያውያን ተገኝተዋል::





ዝግጅቱን በንግግር የከፈቱት በሩሲያ ፌዴሬሽን የኢፌዲሪ ልዩ መልዕክተኛ እና ባለሙሉ ስለጣን አምባሳደር የሆኑት ክቡር አምባሳደር ግሩም አባይ ሲሆኑ አገራችን ኢትዮጵያ የየራሳቸው ታሪክና ማንነት ያላቸው ህዝቦች የሚኖሩባት እና ከ70 በላይ ብሄሮች እና ብሄረሰቦች የባህል ባለቤት እንደሆነችና ኢትዮጵያ ከ3000 ዓመት በላይ ታሪክ ያላት ድንቅ አገር እንደሆነች ገልጸዋል::

በመቀጠልም ባለፉት አመታት ኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ እና አገሪቷ ያላትን ተፈጥሮዊ እና ታሪካዊ መስህቦቿን ለውጭ ጉብኚዎች ክፍት በማድረግ የአገራችን የቱሪስት መስህቦች በውጭ አገር አስጎብኚ ቱር ፓኬጆች  እንዲታቀፉ እንቅስቃሴዎች መደረጋቸውን ገልፀው የሩሲያ ወዳጆች ይህንን እውነታ በመገንዘብ አገራችንን እንዲጎበኙ ጥሪ አቅርበዋል::

አክለውም መንግስት እ.ኤ.አ. ከ2016- 2020 ባሉት ጊዜያት የጎብኚዎችን ቁጥር ከ2 ሚሊዮን በላይ ለማድረስ በሁለተኛው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለቱሪዝም ሴክተር ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን አብራርተዋል::  ከዚሁ ጋር በተያያዘም በተለይም በመሠረተ ልማት፣ በጤና እና በትምህርት፣ በግብርና ግብዓቶች፣ በንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ላይ የተሰጠው ትኩረት በፎቶ ኤግዚብሽን ላይ የተመለከትናቸውንና ሌሎች በገጠሪቷ የአገሪቷ ክፍሎች ነዋሪ የሆኑ ሕዝቦቻችንን ሕይወት ለማሻሻል እየተሰራ መሆኑን ክቡር አምባሳደሩ ገልጸዋል::







በዕለቱ የኢትዮጵያን የተለያዩ ባህላዊ አለባበስ፣ ባህላዊ ምግቦች፣ ባህላዊ የቡና አፈላል ሥነሥርዓት እና የአገራችን ጣዕመ ዜማዎች ቀርበው ለዝግጅቱ ድምቀት በመስጠት ፕሮግራሙ ተጠናቅቋል።

**ኢፌዲሪ ኤምባሲ**
**<u>ሞስኮ</u>**